ግልጽ ደብዳቤ

ለተከበሩ ኢፌዲሪ ጠ/ሚ አብይ አህመድ (ዶ/ር).

ዘ - ዳግም ኢትዮጵያ

ዶ/ር አብይ ከ ሺህ በላይ ኢትዮጵያዊ እስረኞች የሚገኙባትን ሳውዲን በመጎብኘት እስረኞች እንዲፈቱ ጠይቀዋል እንዲሁም በህክምና ስህተት ከ 12 አመት በላይ ኮማ ውስጥ ለነበረ ህፃን ካሳ እንዲያገኝ አስደርገዋል በተጨማሪ በቅርቡ በጎረቤት ሀገር ሱዳን እና ኬንያ በተመሳሳይ በተለያዩ እስር ቤቶች እሚማቅቁት ኢትዮጵያውያን ከእስር አስፈትተው አስደስተውናል በመጨረሻም ተዘርዝረው የማያልቁ መልካም ጅምሮች እና እቅዶችን በሚያምር አንደበተዎ አሳውቀውን ጮቤ አስረግጠውናል።

ነገር ግን በሀገራችን በተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች በመተሳሰብ አብሮ ሚኖረው አማራ በዘሩ ብቻ ተለይቶ ሲገደል ፣ ከነ ነብሱ ሁለቱ አይኖቹን በማውጣት ብልቱን የሰለቡት እና እጅግ ዘግናኝ ምንአልባት የሰው ልጅ በመሰል ፍጡሩ ላይ ያደርገዋል ተብሎ በማይታሰብ ዘግናኝ ድርጊት የተፈፀመበት የ14 አመቱ አበጥር ወርቁ ላይ በቤንሻጉል ጉምዝ ክልል የደረሰው ጥቃት: በርካታ አርሶ አደሮች ከመሬታቸው: ከሞቀ ቤታቸው በገዛ አገራቸው እንደባዳ በመባረር በየቤተክርስቲያኑ እና በየ ጎዳናው ለወደቁት ወገኖችዎ ለምን ምላሽ ለመስጠት አቃትዎ !

አሁንም ይህ ድርጊት ተስፍፍቶ አምቦ እና ኦሮሚያ ክልል በርካታ የአማራ ተወላጆች እንዲሁ ከቤት ንብረታቸው በመፈናቀል ጎዳና ወድቀዋል:: የተከበሩ ጠ/ሚ ለዚህ አፋጣኝ ምላሽ እማይሰጡ ከሆነ ደጋግመው ድምፅዎን ከፍ አድርገው ስሟን ኢሚጠሯት ውድ የሀገራችን ህልውና አደጋ ላይ ናት እና ባፋጣኝ ተጎጅዎች ወደ ቀዩአቸው እንዲመለሱ የጠፍው ሀብት ንብረት ካሳ እንዲከፈላቸው ፤ በተለይ ደግሞ እሄን እኩይ እጅግ ሰይጣናዊ ድርጊት የፈፀሙ ተልኮ የሰጡ ባለስልጣናት እና ግለሰቦች ተጣርቶ በህዝብ ፊት የማያዳግም አስተማሪ ቅጣት እንዲቀጡልን እናሳስባለን!!!

ይህ ካልሆነ ግን የህዝቡ አፀፌታዊ ምላሽ ከባድ እንደሚሆን ከውዲሁ አሳስበወታለው!!!

የ አይትና አባቶቻችንን ታሪክ እንደምንደግመው ከወዲሁ ይታወቅልን !

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

የኢትዮጵያ ህዝብ ብሄራዊ ፓርቲ!!!

ዘ - ዳግም ኢትዮጵያ

EPNP.INFO



ኢ ሕ ብ ፓ
የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY